# የመጀመሪያ የሂሳብ ክህሎቶች ምንድን ናቸው?

**ብታምኑም ባታምኑም፣ ትናንሽ ልጆች የተፈጥሮ የሂሳብ ሊቆች ናቸው!** በጣም ትንንሽ ልጆች መቁጠር ከመማራቸው በፊት እንኳን መጠንን መለየት ይችላሉ። ልጆች በእለት ተዕለት ገጠመኞቻቸው እና ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ በዙሪያቸው ያለውን አለም በመቃኘት ለሂሳብ እየተጋለጡ ነው። ለታዳጊ ህጻናት እና በጣም ትንንሽ ለሆኑ ልጆች፣ የሚረዱ የመጀመሪያ የሂሳብ ክህሎቶች ማነጻጸርን፣ መለካትን፣ የጠፈር ግንኙነቶች እና መቁጠር ሊያካትት ይችላል!



## የሚያስፈልጉት ለምንድን ነው?

በህይወት የመጀመሪያዎቹ ጥቂት አመታት፣ ልጆች ከፍተኛ ጽንሰ ሃሳቦችን ለማዳበር የሚደግፉ፣ የሂሳብ መሰረታዊ ቋንቋን ይማራሉ ለምሳሌ መደመር እና መቀነስ፣ ማስላት እና መከፋፈል።

## ለመርዳት ምን ማድረግ ይችላሉ?

የሂሳብ ቋንቋ መጠቀም! እንደ ወላጆች እና ተንከባካቢዎች፣ በየቀኑ መደበኛ ተግባሮቻችን በሙሉ ሂሳብ እንጠቀማለን። ተግባሮችዎን እና የአስተሳሰብ ሂደቶችን ለመግለጽ የሂሳብ ቋንቋን መጠቀም ህጻናት ዋና ዋና ለሆኑ የመጀመሪያ የሂሳብ ጽንሰ ሃሳቦች እንዲጋለጡ ያደርጋል። እነዚህን የሂሳብ ቃላቶች፣ እና ሌሎችም፣ በቀን ውስጥ ይጠቀሙ!

- ትልቅ፣ ትንሽ፣ በጣም ትንሽ፣ ግዙፍ፣ መካከለኛ
- ረጅም፣ አጭር፣ ከባድ፣ ቀላል
- ከላይ፣ ከታች፣ ቅርብ፣ ሩቅ፣ ከኋላ፣ ከጎን
- አደገ፣ ቀነሰ፣ ሙሉ፣ ባዶ
- የበለጠ፣ ያነሰ፣ እኩል
- መጀመሪያ፣ ቀጥሎ፣ በፊት፣ በኋላ

# የመጀመሪያ ሂሳብ ክህሎቶችን ለመደገፍ ጠቃሚ ምክሮች

## የምግብ ሰዐታት

“**ተጨማሪ** ፖም ትፈልጋለህ?” “**ሁሉንም** ወተትህን ጠጥተሃል! ኩባያህ **ባዶ** ነው!”





## የጨዋታ ጊዜያት

**ትላልቆቹን** ብሎኮች **ከታች** እንዲሁም **ትናንሾቹን** ደግሞ **ከላይ** እናስቀምጥ። “የጭነት መኪኖቹን በአንድ መስመር እና መኪኖቹን በአንድ መስመር አስቀመጥካቸው። የትኛው **ይረዝማል**?” “ደረጃዎቹን**ወደ ላይ** እየወጣህ ነው እና ሸርታቴውን **ወደ ታች** ተንሸራተክ ትወርዳለክ!”

## እለታዊ መደበኛ ተግባራት

**መጀመሪያ**፣ ፒጃማ እንለብሳለን፣ **በመቀጠል** ጥርሳችንን እንቦርሻለን።” “ኩባያውን**ለመሙላት** ስንት ማንኪያ ውሃ **እንደሚያስፈልግ** እንይ!”



DCPS የቅድመ ልጅነት ትምህርት

@dcpsearlychildhood

readyforprek.org

**ድህረገጻችን ይጎብኙ**